VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH
To protect the health and promote the well-being of all people in Virginia.

# የዊንዶው ሕክምና ለሳምባ ነቀርሳ (TB) ከተጋለጡ በኋላ

## ወላጆች ማወቅ ያለባቸው



**ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ከኢንፌክሽን በኋላ በፍጥነት ከባድ በሆነ የTB በሽታ ዓይነት የመጠቃት አደጋ ላይ ናቸው**

### የዊንዶው ሕክምና የመጀመሪያውን ኢንፌክሽን እና ወደ በሽታ የመዛባትን ሁናቴ ሊከላከል ይችላል

**በሕፃናት ላይ የሚታዩ የTB በሽታ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:**

- ሳል
- የሕመም ወይም የድካም ስሜቶች
- ከባድ ድካም
- የሚያሰምም ስሜት
- ክብደት መቀነስ ወይም ቅጥ ያጣ የክብደት መጨመር
- ትኩሳት
- በለሊት ማላብ

ልጄ አይሶኒዚድ እንዲወስድ እንዴት ልረዳው እችላለው?

- ክኒኖች ተሰባብረው ውሃ ውስጥ ሊሟሙ ይችላሉ። ማታ በእንቅልፍ ጊዜ ክኒኖችን መስጠት ሊከተል የሚችለውን የሆድ አለመመቸት ሊያስወግድ ይችላል። የተሰባበረውን
- ክኒን ልጅዎ ሊወዳቸው ከሚችሉት ነገሮች ከሚከተሉት ጋር በትንሹ ይቀላቅሉት:

**ሙዝ ታሽቶ**

**የፖም ጭማቂ**

**ገንፎ ነገር**

**እርጎ**

**ልጄ የዊንዶው ሕክምና ከመጀመሩ በፊት መሆን ያለበት ምንድን ነው?** ልጅዎ የዊንዶው ሕክምና ከመጀመሩ በፊት፣ የምልክት ማጣሪያ፣ የአካል ምርመራ፣ የደረት ራጂ፣ እና የቆዳ ወይም የደም ምርመራ ለTB ኢንፌክሽን ያደርጉላቸዋል

**የልጄ የTB ምርመራ ውጤት ኔጌቲቭ ከሆነ ሕክምና ለምን አስፈለገ?**

ልጅ ለTB ከተጋለጠ በኋላ በሽታው ፖዘቲቭ ሆኖ በልጁ ላይ ለመታየት ጊዜ ይወስዳል። ዊንዶው ተብሎ የሚጠራው ሕክምና፣ ልጅዎ በእርግጥ በበሽታው የተጠቃ መሆኑ እና አለመሆኑን እስኪረጋገጥ ድረስ መድሐኒቱ ልጅዎን በመጠበቅ የታወቀ ነው። ታዳጊ ሕፃናት በፍጥነት አደገኛ ወደሆነው የTB ዓይነት የመሸጋገር እድላቸው እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ፣ በወቅቱ እነርሱን መንከባከብ በጣም ጠቃሚ ነው።

**ልጄ በ8-10 ሳምንታት ውስጥ ሌላ የTB ምርመራ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?**

ልጅዎ በበሽታው ተጠቅቶ ከሆነ የልጅዎ ሰውነት በ8-10 ሳምንታት ውስጥ ለበሽታው ግብረ መልስ የመስጠት በቂ ጊዜ ይኖረዋል። ሁለተኛው ምርመራ፣ ልጆቹ ሕክምናውን መቀጠል እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው ወይም በበሽታው ያልተጠቁ ከሆነ ሕክምናውን ማቆም እንዳለባቸው ይነግረናል።

**ትልቁ ልጄ የዊንዶው ሕክምና የማያስፈልገው ለምንድን ነው?**

ከትንንሾቹ ልጆች እና ከሕፃናት አንፃር ሲታይ ትልልቆቹ ልጆች ወደ የከፋ የቲቢ በሽታ በፍጥነት የመሸጋገር እድላቸው ያነሰ ነው።

### ሊያጋጥሙ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች:

- መለስተኛ ማቅለሽለሽ/ትውከት/የሆድ
- አለመመቸት
  በእጅ ወይም በእግር አካባቢ የቁርጥማት ዓይነት ስሜት
- - ይህን ለማሻል የልጅዎ ዶክተር ቫይታሚን B6

### የልጅዎን ዶክተር መቼ ነው ሊጠሩት የሚገባ:

- ልጅዎ በየትኛውም የፊት አካባቢ እብጠት፣ ሽፍታ፣ ወይም ብጉር ነገር ካሳየ ወይም የመተንፈስ ችግር ሲያጋጥመው
- ልጅዎ ከ24 ሰዓታት በላይ የሚታይ ማቅለሽለሽ/ትውከት ካለበት
- የልጅዎ ቆዳ ብጫ የመሆን ምልክት ካሳየ ወይም በዓይን ላይ የመንጣት ነገር
- ከታየ
- ልጅዎ ቀለሞችን የማየት ወይም የመለየት ችግር ከታየበት